# አስመሪኖ

አብርሃም በየነ

የቢሸፍቱን ሰብል አስጉዘን አሥመራ

እየጠረጠርን እሸቱን ሽምብራ

ባቄላ ነው ስንል ከፊላችን አተር

ቀደም ባርባ ጉጉ አረካና ወተር

በደሴና አጋሮ ባደባባይ ጎንደር

ያየነውን አይተን በቡርቃ ዝምታ

በቀጭኑ ፈትለን ለደራሲው ኩታ

ባገር ስም ሽምነን ባለበስነው ጃኖ

ቢሸፍቱና ሽገር ሲኖር ተዘባኖ

በዘር ነክ ደዌ ህሊናውን ስቶ

ራሱን አጠፋ በብዕር ጫፍ ወግቶ።

***...................................... ***

መጠንቀቅ ነው እንጂ ምንድን ነው መጃጃል

የብርሃኑ ጦር እሳት ነው ይፋጃል፤

እሳት ነው ይፋጃል የብረቱ አለሎ

ያንዳርጋቸው ፅጌ የጦር ሜዳ ውሎ

ድል አርጎ ሲመለስ አቁስሎና ገድሎ

እንጀራ ያመጣል ባፈሙዝ አብስሎ።

ጥቅምት 2006

abraham3106@comcast.net

............................//........................................